# ከዋናው መስሪያ ቤት የሞጡት እንግዳ
# ክፍል ሶስት

ከበልጅግ አሊ

ጉመሮ ዝምታ ውጦታል። ምንም ነፍስ ያለበት አይመስልም። ሻይ ለቃሚዎች ዝናብ ሰላልነበር ዝናብ የሚመጣበትን ቀን መቁጠር ጀምረዋል። ሃሳብና ትካዜ በሁሉም ሠራተኛ ገብቷል። ከሩቅ የናስር ትራክተር ያጓራል። የመብራት መስጫ ሞተሩ የማያቋርጥ ድምፅ ስለተለመደ ማንም አይሰማውም። ሞተሩ መጮሁን የሚሰሙት አዲስ ጉመሮን ለመጎብኘት የመጡ ሰዎች ብቻ ናቸው። የኤሌትሪክ ሠራተኛው ታደሰ የተለመደውን ፀሎቱን ጮክ አድርጎ እየተናገረ ግቢውን ይዞራል።

**„ለየሰው እንደየስራው ለዕፅዋቱና ለእንስሶቹ አዝንብላቸው“**

**በ**ግቢው ውስጥ ጮክ ብሎ የሚናገር አንድ ታደሰ ብቻ ነው። ታደሰ „ድኩላዎቹ እንኳ ውሃ ቢጠማቸው ከሰው ቀረቡ። ውሃ የልማት ምንጩ ፣ የጥፋት ምንጩ ፣ የፍቅር ምንጩ ፣ የደስታችን ምንጩ ፣ የሃዘናችን መግለጫው ውሃ ነው። ጌታችን እባክህ ለኛ እንደየስራችን ፣ ለሻዩ ፣ለዛፉ ፣ለሳሩ ፣ ለቅጠሉ ፣ ለድኩላው ፣ ለዝንጀሮው ፣ ለዎፎቹ ፣ ለማይናገሩት ፣ ሰው ለማያሰቀይሙት ፣ ለፍጥረቶችህ ዝነብላቸው። እግዚዮ እንበል እግዜር ቢታረቀን እንለምን“ ብሎ እንደተለመደው ይጮሃል።ግን ማንም የሚሰማው የለም። እንደ ኤሌክትሪኩ ሞተር የታደሰ ጩኸት የተለመደ ስለሆነ ማንም ጉመሮ የኖረ ልብ ብሎ አያዳምጠውም።

**ሊ**ቁ ቅዳሜ ቅዳሜ ጠዋት እንደለመደው ወንበሩን አውጥቶ ከበረንዳው ላይ ተቀምጦ ማሰብን እሮብ ገበያ ከመጣበት ግዜ ጀመሮ የለመደው ጠባዩ ነው። ያ ያረጀ ሰማይ ያለውን ውሃ ሁሉ ለቆ እንደጨረሰ አንድም ዳመና በላዩ ላይ አይታይም።ባለፉት አመታት ዝናብ ሳያቋርጥ በሚጥልበት ግዜ ከበረንዳው ቆርቆሮ ላይ የሚወረወረውን ዝናብ እየተመለከተ አንዴ እየሳቀ አንዴ እየተከዘ አንዳንዴ ደግሞ ብቻውን ይነጋገር ነበር።ዛሬ ግን ጥርት ያለውን ሰማያዊ ሰማይን እያንጋጠጠ እየተመለከተ የሰማዩ መጨረሻ የት እንዳለ እያሰበ ሃሳቡ እሩቅ እየሄደበት ሆድ እየባሰው አይኖቹ እንባ እያቀረሩ በቅርብ ግዜ አብሮአቸው የነበሩት ጓደኞቹ የት እንዳሉ እያሰበ አንዳንዴ እንደ መበሳጨት አንዳንዴ ደግሞ ጮክ ብሎ በመሳደብ ባለቤቱን ያስደነግጣት ነበር።

**ሊ**ቁ መጀመሪያ ሰሞን እሮብ ገበያ የህይወት እጣው ሆኖ እንደመጣ ለግዜያዊ ችግሩ ማለፊያ መደበቂያ ቦታ ሆኖ ስላገኘው ይደሰትበት ነበር። ያም ሆኖ ቀኑ እየገፉ ያ የጭንቅ ዘመን የመጨረሻ ጫፉ አልታየው ሲለው፣ብቸኝነቱ ደግሞ ሲያንገላተው፣ ሊለምድ ያልቻለው የገጠር ኑሮ አዲስ ሆኖ ለመልመድ ሲያዳግተውና የቅርብ ግዜው ትዝታው የተለያቸውን ጓዶኞቹን እያሰበ የሃሳብ ማዕበል ሲያናውጸው ያ የሚያምንበት የወደፊት ብሩህ ተስፋ ደብዛው ሲጠፋበት ጊዜ ቢገፋልኝ ብሎ በሚያስተምርበት ትምህርት ቤት ውስጥ አንዳነድ ነገሮችን ለማሻሻል ሙከራ እያደረገ ኑሮውን ጀመረ።

**ሊ**ቁ እሮብ ገበያ እንደመጣ የዚህ አገር እህል ውሃዬ በቅርብ ቀን ተገባዶ ያልቃል በሚልና በአስተሳሰቡ ሊቀበለው የማይችለው ገረድ ቀጥሮ መኖርን በመቃወም የቤት እቃውን እራሱ ገዝቶ ምግቡን ማዘጋጀት ጀመሮ ነበር። ቢሆንም ግን ያደረገውን ሙከራ ብዙም ግዜ አልቆየም። እሳት ማያያዝ እያቃተው አይኑን ጭስ እያስለቀሰው ስቃዩ ሃሞቱን ሲቆልፍበት ባይበላስ ብሎ አንድ ሁለት ሳምንት ዳቦ በሻይ ሲበላ ከርሞ ነበር። ታዲያ አንድ ቀን ጎረቤቱ የነበሩት ሽማግሌ ስላምታውን ስለሚወዱትና ስለሚያሳዝናቸው አንድ ቀን ሰራተኛ ቢቀጥር እራሱን እረድቶ ሌላም አንድ ሰው እንደሚረዳ ስለ አሳሰቡት እሱ ከሚያስበው ውጭ ለካ ሌላ መርዳት እችላለሁ በሚል ሰራተኛ መፈለግ ጀመረ።

ለአካባቢው ሰው ሁሉ ሰራተኛ የት ይገኛል ብሎ ሲጠይቅ አስተማሪ የሚበላውን የፈረንጅ ምግብ መስራት የምትችል እዚህ መች ይገኛል ብለህ እዛው ጅማ ሄደህ ከጋሜ ካላመጣህ ወይም ምንአልባት እድል ከገጠመህ ደግሞ ከመቱ ካላገኘህ። ባስታና መኮሮኒ ነው የዘንድሮ አስተማሪ የሚወደው እሱን ደግሞ መስራት የሚችል እዚህ ገጠር የት ይገኛል ብለህ እያሉ ተስፋ አስቆረጡት። ሊቁ ደግሞ ወደ ከተማ ካልተገደደ በስተቀር የሚያውቀኝ ሰው ያገኘኛል በሚል መሄድ አይፈልግም ነበር። ጅማ ደግሞ ብዙ የአዲስ አበባ ሰው ስለሚገኝበት የማይታሰብ ነው።

አንድ ቀን ታዲያ እንደለመደው በረንዳው ላይ ተቀምጦ ሲተክዝ ጎረቤቱ የነበሩት ሽማግሌ መጥተው ሰራተኛ እንዳገኙለት ከነገሩት በኃላ እንጀራ አባቷ ፈቃደኛ መሆኑንና ነገር ግን ልጅቷ ፈቀደኛ መሆኑዋን መጠየቅ እንዳለባቸው ነገሩት። ሊቁም ልጅቷ እሰው ቤት ሰርታ እንደምታወቅ ቢጠይቃቸው እሳቸውም ስው ቤት እንኳ ስርታ አታውቅም ግን ጎሬ እየተመላለሰች ትማር እንደነበር ነገሩት። በዚህ ንግግራቸው ልጅቷ እስከ ሰባተኛ ክፍል ቢያንስ እንደተማረች አወቀ። ምክንያቱም እሮብ ገበያ እስከ ስድስተኛ ክፍል ድረስ ትምህርት ቤት ሰላለና ሚኒስትሪን ያለፉ ወደ ጎሬ እንደሚሄዱ ስለሚያውቅ ልጅቱን ለማየት ቸኮለ። ለምን ትምህርቷን አቋርጣ ስራ ለመስራት ፈለገች ብሎ ቢጠይቃቸው እሳቸው ምክንያቱን እንደማያውቁ ነገር ግን ትላንት ጠጅ ቤት ከእንጀራ አባቷ ጋር እንደተነጋገሩ ነገሩት። ከትንሽ ግዜ በኃላ ሽማግሌውና እንጀራ አባቷ መጥተው ከሊቁ ጋር ስለስራውና ስለደሞዙዋ ከተነጋገሩ በኃላ እንጀራ አባትየው ልጅቱን ይዞ እንደሚመጣና የአንድ ወር ደሞዝ በቅድሚያ እንደሚፈልግ ለሊቁ ነገረው።

በበነጋታው አንዲት የቀይ ዳማ የሆነ ክብ ፊትና የደስደስ ያላት ልጅ በማዳበሪያ ጆንያ ልብሷን እንደያዘች የእንጀራ አባትየው ይዞ መጣ።ሊቁ ልጅቷን ገና ሲያያት ሃዘን ተሰማው። በልቡ ስንት እንደዚች አይነት ወጣቶች ትምህርት ቤት በመሄጃቸው ሰአት በየሰው ቤት በግርድና ተቀጥረው ፍዳቸውን ሲቆጥሩ ይውላሉ ብሎ አዘነ። ቢሆንም ግን ልጅትየዋን ተቀብሎ አባትየውን ካሰናበተ በኃላ ቤቱንና የቤቱን እቃ አሳያት።በመቀጠልም በሚቀጥለው ሳምንት ወደ ጎሬ ወጥተን የጎደለውን እንገዛለን። እዛኛው ክፍል ውስጥ ያለው አልጋ ላይ አንቺ ትተኛለሽ። እኔ ግን መሬት መተኛት ስለምወድ እሳሎን ያለው ፍራሽ ላይ ነው የምተኛው ሲላት ልጅቷም ደንግጣ አይሆንም እኔ ማድቤት ሳር ጎዝጉዤ ነው የማድረው አለችው። ሊቁ ግን አይሆንም ባይሆን አልጋው ላይ መተኛት ካልፈለግሽ እጓዳው ውስጥ አስተካክይና መሬት ላይ ተኚ ብሎ አዘዛት።

ሊቁ እቤት ውስጥ የሚያጫውተውና ምግቡንም የሚሰራላት ስላገኘ ቢደሰትም ግን ልጅቷ ትምህርቷን ስላቋረጠች ለምን አትማርም ብሎ ሁል ግዜ ይረበሽ ነበር። ታዲያ አንድ ቀን ጌጤ ለምን ትምህርት አቆምሽ አላት። ቢቸግረኝ ነዋ ጋሼ አለችው። ይዞኝ የመጣውእንጀራ አባቴ እንጂ አባቴ አደለም። ይሁን ብሎ እስከስምንተኛ ክፍል እንድማር ፈቀደልኝ። ስምንተኛ ክፍል ሚኒስትሪ ስፈተን ብዙም ሰላለጠናሁ ወደቅሁኝ ካዛም እንጀራ አባቴ ሻይ ለቀማ እየሰራሁ ቤተሰቡን እንድረዳ ስላለ ትምህርቴን አቋረጥኩ። ለነገሩ ትምህርት ማቋረጤ ደስ አለኝ። ከሮብ ገበያ እስከ ጎሬ በእግሬ እየተመላለስኩ መማር አልቻልኩም ነበር። በዚያ ላይ ደግሞ በየመንገዱ እየጠበቀ የሚደባደበውን ጎረምሳ አልቻልኩትም።

ሊቁ በትርፍ ግዜው ከጌጤ ጋር መጨዋወትን እየወደደው መጣ። ጌጤ ካልጠየቋት ያማትመልስ ብትሆንም እንዳደገችበት የገጠር ልጅ አትመስልም ነበር አንዳንድ ግዜ የምትሰጠው መልስ ሊቁን ከሷ የማይጠብቀው እየሆነ በጣም ይደነግጥ ነበር። እሱ ቤት ከተቀጠረች ከስድስት ወር በኃላ ልክ እንደጓደኛው ስለስራው ፣ስላለፈ ህይወቱ ይነግራታል።እሷም ደግሞ በጥሞና ትሰማለች። አንዳንድ ግዜ ሊቁ ካመሸ በረንዳ ተቀምጣ ትጠብቀዋለች። በስድስት ወር ውስጥ አለባበሱዋም ተቀየረ። ሰውነቷም ከጉስቁልና ተመልሶ ተስተካከለ። ሊቁ ምግብም ሆነ ማንኛውንም ነገር ከሷ ተልይቶ አያደርግም። ጎሬ ገበያ ስትወጣ እንኳ እስከምትመጣ ይጠብቃታል።

አንድ ቀን ሊቁ በጠዋት ተነስቶ እንቅልፍ ጨርሶ ቀኑ ቅዳሜ ሰለሆነ በረንዳ ላይ ተቀምጦ እቤት ውስጥ ጉድ ጉድ የምትለውን ጌጤን ይመለከታል። የእግሩን ጥፍር እየቆረጠ ስለ ጌጤ ማሰብ ጀመረ። „ንፁህ ምንም የማታውቅ ፣ ክፋት

የሌላት“ ብሎ ጮክ ብሎ ተናገረ። ጌጤ ብቻውን መነጋገሩን ስለለመደችው ምንም ሳይመስላት ስራዋን ቀጠለች። „የከተማውን ተንኮል የማታውቅ ፣ ከጎሬ የሰፋ ከተማ ያላየች ፣ አለም ጉመሮና ጎሬ ብቻ የሚመስሏት፣ እንዴት የታደለች ፍጡር ነሽ፣ አለምን ባለማወቅሽ ደስተኛ ነሽና ተደሰቺ፣ እንደኔ አለምን ብታውቂያት ፣አለም በውስጥዋ ያዘለችውን ጉድ ብታይ ፣ የሰውን ጨካኝነት ብትመለከቺ ኖሮ ምን ያህል አለምን በጠላሻት ነበር“ ብሎ እንደገና አልጎመጎመ።

**ጌ**ጤ ሊቁ ምንም ሳያስበው የምትሰራውን ሁሉ አቁማ አጠገቡ መጥታ „መከራና ስቃይ በከተማ ብቻ ያለ መስሎህ ከሆነ ተሳስተሃል ጋሼ። አንተ ምንአልባት እዚህ ገጠር መኖርህን እንደስቃይ ትቆጥረው ይሆናል። ከሆነም እንግዲህ እኛ በስቃይ ተፈጥረን ፣ በስቃይ ተወልደን ፣ በስቃይ አድገን በስቃይ እንሞታለን። ክፉት ጨካኝነት በከተማ ብቻ የተወሰነ መስሎ ከታየህ ልክ አደለህም። እንደግዜውና እንደ ሁኔታው ይለያይ እንጂ በሁሉም ቦታ ጨካኝም፣ ክፉም አሉ። እኔ ዛሬ እዚህ አንተ ጋር በመቀጠሬ ደስተኛ ነኝ። ነገ ብታባርረኝ ደግሞ የሚደርስብኝን ስቃይ አውቀዋለሁ። ግን እኔ ህይወትን አላማርርም እንደ አመጣጡ እቀበለዋለሁ። ግን እኔን የሚያሳስበኝ ለከተማ ያለህን ፍቅር ስመለከተው እኔን ጥለኸን ወደ ከተማ ብትሄድ የሚደርስብኝን የኔን መስቃየት እረስቼው የአንተ ሁኔታ ተሳክቶልህ እንዲህ ወደምትናፍቀው አዲስ አበባ እንድትሄድ ነው ምኞቴና ፀሎቴ። የገጠር ኑሮ ለአንተ አይሆንም አለችው።ምንም አዲስ አበባን ባላውቀውም እንተ በነገርከኝ ስጠላውም ስውደውም ከረምኩ። አሁን ግን ለአንተ ሌላ ነገር የሚያስደስትህ ይኖራል ብዬ ስለማላምን በየምሽቱ እፀልይልሃለሁ“።

**ሊ**ቁ ከመደንገጡ በቀር ምንም መልስ ሊሰጣት አልቻኮለም። እራሱን አረጋግቶ እንዲህ አላት። „ጌጤ ከዚህ ቤት በምንም ምክንያት ቢሆን እንደማትወጪ ለአረጋግጥልሽ እወዳለሁ። ስለከተማ ያልሽው ይህንን ያህል የታዘብሽን አልመስለኝም። አዎ የተወለድኩበት ፣ እትብቴ የተቀበረባትን አዲስ አበባን በእኔና እኔን በመሰሉት ላይ ሳትጨክንብን በፊት እወዳት ነበር። አዲስ አበባ በኛ ላይ ጨከነች። እንዳልወለደችኝ አሳልፋ ሰጠችን። ኳስ እንዳለተተጫወትንባት ፣ አዱ ገነት ብለን እንዳላቆላመፅናት አንድ ቀን እንኳ ልትደብቀን ተሳናት ፣ እሬሳችንን ተቀበለች ፣ ደማችንን ጠጣች። አንቺ እንደምትይው ፍቅሯ ሳይሆን ጥላቻው እንዳልረሳት አደረገኝ። እሮብ ገበያን በስቃዬ በችግሬ ታቅፋ መጠጋዬ ስለሆነች እወዳታአለሁም አከብራታለሁም። ግን ገና ብዙ የምነግርሽ አለና ሆዴ ሳትሰለቺ ስሚኝ አላት“።

„**ጋ**ሼ መቸስ ትታመማለህ ብዬ አስቤ ይሄን ተናገርኩ እንጂ እንዳንተ ሁሉን የማውቅ አደለሁም። ጓደኞቼ ሁሉም አገቡ እኔ ግን አንተን አምኜ እዚህ ሰኖር አንድ ቀን ከፍቶኝ አላውቅም ነበር። ትላንትና እንጀራ አባቴ መጥቶ የቡና መልቀሚያ ግዜ ስለደረሰ ስራዬን አቁሜ ቡና ለቀማ እንድሄድ ጠየቀኝ። እኔ ግን አንተን ጥዬ መሄድ እንደማልችል ስነግረው እሱ በሌላ ወሰደውና ጓደኞችሽ ሲያገቡ አንቺ ከሱ የማትለይው ምን አቅምሶሻል ብሎ የለመደውን ሁሉ ሰድቦኝ ሄደ። በኃላም እናቴን ልኮ እንድትመክረኝ አደረገ። አሁን ቡና ለቀማ ባልሄድ እናቴን እየደበደበ ያሰቃያታል። ስለዚህ ለአንድ ወር ፍቀድልኝና ቡና ለቅሜ ልመለስ „አለችው።

**ሊ**ቁ አይንገራት እንጂ ካለእሷ ለመኖር እንደማይችል ገብቶታል። ትንሽ ግዜ ካሰበ በኃላ „አይሆንም አትሄጂም አላት። በፍፁም አትሄጅም። ከአሁን በኃላ ማንም በአንቺ ህይወት አያዝም። የሚፈልገውን ገንዘብ እንከፍለዋለን እንጂ አንቺ አትሄጂም“። ብሎ ቀና ብሎ ሲያያት የእንባ ስቃይ ይዞት ትንሰቀሰቃለች። አጠገቧ ሄዶ ተቀምጦ ያባብላት ጀመር። እንባዋን እየጠረገላት አይዞሽ ሲላት የስውነቷ ሙቀት በስውነቱ ውስጥ እየገባ ሙቀት ተሰማው። ወደ እሱ አቅርቦ እቅፍ ሲደርጋት እራሱዋን እትከሻው ላይ አድርጋ „ጋሼ መሄድ አልፈልግም ግን መቅረትም ደግሞ አልችልም እናቴን ያሰቃያታል“ አለችው። እሱም ግዴለሽም ብልሃት እንፈልጋለን ሲላት ቀና ብላ ፈገግ ስትልለት ለመጀመሪያ ግዜ በደንብ ያ ደስ የሚለውን ክብ ፊቷን ተመለከተ፣ በለቅሶ የአበጡ ከንፈሮቹዋን ልብ ብሎ ከአየ በኃላ ከውስጥ አንድ ነገር ተሰማው። ሳማት ሳማት የሚል ሰሜት መጣበት። ምንም ሳያስበው ጉንጯቿን ሳማት።ሲስማት የምትርቀው መስሎት ነበር ግን የባሰ ቀረበቸው። አቀፋት አቀፈችው ፣ ሳማት ሳመችው። ሰውነቱን ሞቀው ሞቃት።የባሰ ቀረባት ቀረበችው።እየደጋገመ ሳማት ሳመችው። እንባዋ የፈሰሰበት ጨው ጨው የሚለውን ፊቷን ላሰው። በደከመ ድምፅ ከዚህ የትም አትሄጂም አላት እሷም ልለይህ አልፈልግም አለችው። ህይወት በሊቁና

በጌጤ ልብ ውስጥ አዲስ የደስታ ምዕራፍ ከፈተች። ይዞአት ተነሳና ወደ ጓዳ ገቡ ለብዙ ግዜ ሳይወጡ እዛው ቆዩ። ከዛ ሲወጣ ብቻውን ብራምባር ዘፋኑ። ጌጤም ለብዙ ግዜ ከጎረምሳ ጋር የተጣለችበትን ክብሯን ለምትወደው ለምታምነው በመስጠቷ የደስታና ሃዘን የተቀላቀለበት ቀዘቃዛ ለቅሶዋን አልጋው ላይ አነባች። እስቲ አምጡት የደሙን ሽማ እንድንስማማ ሲባል ታሰባት። ሊቁ ከሳሎን ተመልሶ ወደ ጓዳ ገብቶ ለምን ታለቅሺያለሽ ብሎ ጠየቃት። በደከመ ድምፅ ታገባኛለህ በላ የሚረብሻትን ጠየቀችው።

**በ**ደንብ ነዋ ሆዴ አገባሻለሁ እንጂ ምን ጥያቄ አለው አላት።ናስር ዛሬ ስለሚመጣና ጫት ስለምንቅም ቤቱን አዘጋጂ እዛም ላይ ከእሱ ጋር ስለኛ ጉዳይ እንነጋገርበታለን ብሏት ወጣ። ጌጤም ተነስታ ቤቱን እያዘጋጀች ከጓደኞቿ እኩል ባል፣ ያውም አስተማሪ፣ ከአስተማሪም ሊቁን በማግኘቷ አምላክን አመስገነች።ፊቷ በፈገግታ ተሞላ። አምላክ ለዚህ ቀን ሰላደረሰከኝ ምስጋና ይግባህ አለች።

ይቀጥላል

በልጅግ አሊ